PANORMA # XXXI

**ሰኔ** 27 **ቀን** 2000 **ዓም**

# ኢትዮጵያና የታሪክ እንቆቅልሾች

*የታሪክ ምፀትና እንቆቅልሽ ሰለባዎች ከሆኑት በጣም ጥቂት የዓለም ሀገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ ሀገራችን ግምባር ቀደም ነች ብንል ከእውነት የራቀ አባባል ነው ሊባል የሚቻል አይሆንም፡፡ ከተባለና የሚያሳምነንም ከተገኘ፥ ይቅርታ ከመጠየቅ ወደ ኋላ አንልም፡፡ እኛ ግን ይህን አባባላችን፥ የተቻለንን ያህል በማስረጃ እያስደገፍን ለመግለጽ መሞከራችን አይቀርም፡፡ ይህን የምናወሳውም ደግሞ፥ ለሀገራችን፥ ለሕዝባችን ለታሪካችን፥ ለወደፊት ዕድላችንና ራዕያችን ካለን መቆርቆርና መቆጨት እንጅ፥ የሞራል ሥልጣኑ የኛ ብቻ ነው ከሚል ግብዝነት አይደለም፡፡ በዕርግጥ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተበድሏል፥ ተጠቅቷል፥ ግፍና መከራ ዘንቦበታል፡፡ ከዚህም የተነሳ፥ ቁጭት አለበት፤ ሰቆቃ አለበት፥ የቅርብ ጎረቤትም ይሁን የሩቅ ዘመድ የለውም፡፡ የሚያምናቸው መሪዎቹ በየጊዜው ይጎዱታል፥ ይበድሉታል ያዋርዱታል፥ ይጨቁኑታል ይዘርፉታልም፡፡ በመጨረሻም አልሆን ሲላቸው ከድተው፥ ለሌላ በላዔ-ሰብ አጋልጠውት ጥለውት ይሄዳሉ፡፡ በቀውጢ ቀን፥ በወሳኝ ጊዜ፥ ሰማይ ምድሩ በሚደፋበት ወቅት፥ ጉም አድርገውት ይሸሻሉ፡፡ የአምባገነን ሥርዓት አራማጆች በሥልጣን በሚቆዩበት ዘመን፥ <u>ተጠልቶ መፈራትን እንጅ፥ ተወድዶ መከበርን</u> <u>አይፈልጉም</u>፡፡ ዘወትር በሕዝብ ዘንድ የተጠሉ መሆናቸውን ባይዘነጉትም፥ ዘለዓለም ተፈርተው የሚኖሩ ይመስላቸዋል፡፡ ሁል ጊዜ ሕዝቡ ፀጥ ለጥ ብሎ የሚገዛላቸው ይመስላቸዋል፡፡ ኃይላቸው የሚሳሳ፥ ጉልበታቸው የሚደክም፥ ሥልጣናቸው የሚከስም፥ ቀናቸው የሚጨልም፥ ጊዜያቸው የሚያከትም ፈፅሞ አይመስላቸውም፡፡ በሕዝብ አመፅ በአፍ-ጢማቸው የሚደፉ መሆናቸውን ጭራሽ አይታያቸውም፡፡*

*የሕዝብ ኃይልና ሥልጣን፥ የሕብረተሰብ የመጨረሻው ወሳኝ መሆኑ የሚያከራክር ባይሆንም፥ በኢትዮጵያ ሀገራችን ግን ይህ ሃቅ እስከዛሬ ድረስ መከሰት ቀርቶ፥ ሊታለምም አይገባውም ሊሉ የሚቃጡ ብዙ ናቸው፡፡ ህልምን ወደ ዕውነት ለመለወጥ ግን ሕዝቡ የሚሳነው ሆኖ አይቀርም፡፡፡ ግን ይህን ማድረግ የሚቻለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨምግጎ ከያዘው አባዜ ሲላቀቅ ብቻ ይሆናል፡፡ ይህ አባዜ ደግሞ፥ የታሪክ ዕንቆቅልሽና የዘመናት ምፀት ነው፡፡ እነኝህን ቁራኛዎች ማስወገድ መቻል ይኖርበታል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ሁሉን ማድረግ የሚያስችለው ኃይልና ሥልጣን ሊኖረው ሲችል፥ በአምባገነኖች እየተገዛ ይኖራል፡፡ በልቶ ጠጥቶ መኖር የሚያስችለው ሁለንተናዊ የተፈጥሮ ሀብት ሞልቶ ተርፎት፥ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ በማጣት በምፅዋት ዕድሜውን ይገፋል፡፡ በአፍሪካ ተወዳዳሪ የሌለው የሰለጠነ የሰው ኃይል እያለው ያንን ሊጠቀምበት አልተቻለውም፡፡ በመላው ዓለም ተሰራጭቶ ሌላውን የሚያገለግል በተለያየ የሙያ መስክ የሰለጠነ ምሁር እያለው፥*

አልተገለገለበትም፡፡ ይህም ሌላው እንቆቅልሽ ሆኖበታል፡፡ ስንት ጀግና ስትፈጥር የነበረችው ሀገር ዛሬ የወላድ መካን ሆና የባንዳ መንጋ መጫወቻ ሆናለች፡፡ በዘመነ-ቅኝ ግዛት፥ ልዕልናዋ ያልተገሰሰ፥ ድንበሯ ያልተደፈረ ፥ ነፃነቷ ያልተተነኮለ፥ ባህሏ ያልተበረዘ፥ የጀግኖቿ ማንነት የተመሰከረ ሀገር፥ በአሁኑ ጊዜ በዚህም በዚያም ድንበሯን የሚያስደፍር አገዛዝ ተሰይሞባታል፡፡ አብዛኛው የዓለም ሕዝብ በዴሞክራሲ ሥርዓት እየተስተዳደረ፥ ዛሬ በአምባገነን ከሚጨቆኑ ጥቂት ሀገራት የመጀመሪያውን ቦታ ከያዙት ሀገሮች አንዷ ሀገራችን ኢትዮጵያ ነች፡፡ እንዲያው በደፈናው ሀገራችን ኢትዮጵያ የታሪክ ዕንቆቅልሽና የዘመናት ምፀት ሰለባ ነች ከማለት በስተቀር፥ እናም ደግሞ፥ ከነዚህ አባዜዎች ተላቅቃ እንዴት ጤናማ ሀገር ትሆናለች የሚለውን ብልሃት ከመፈለግ በስተቀር፥ ምፀቶቿንና ዕንቆቅልሾቿን ዘርዝረን መጨረስ የሚቻለን አይደለም፡፡

በሌላ ረገድ ደግሞ፥ ምፀቶቹንና እንቆቅልሾቹን ምናልባት እኛው እራሳችን ፈጥረናቸው እንደሁ እንጅ፥ ከዚያም፥ አብረውን እንዲኖሩ ፈቀድንላቸው እንጅ፥ እነርሱ በራሳቸው የችግሮቻችን ምንጮች ናቸው ማለት አይደለም፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን/ያት የውስጥ ችግራችንን ለመፍታት ከመጣራችን አስቀድመን ችግሮቻችንንና ምንጮቻቸውን በሚገባ መረዳት ይጠበቅብናል፡፡ የተማረው ክፍል፥ የፖለቲካ ድርጅቶችና የነቃሁ-የበቃሁ ነኝ የሚለው የኅብረተስብ ክፍል የየግል ችግሩን ራሱ እያስወገደ፥ በራሱ እየተማመነ፥ ከሌላው ወገኑ ጋር ተስማምቶ የጋራ ሀገሩን ችግር በጋራ ለመቋቋም እስካልቻለ ድረስ፥ የሀገራችን መሠረታዊና ውስብስብ ችግሮች ሊወገዱ ቀርቶ ሊቀረፉ ይችላሉ ማለት፤ ቢያንስ እራስን ማታለል ይሆናል፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ ይህን መገንዘብ ማለት፥ ለችግሮቻችን መፍትሄ ፍለጋ የመጀመሪያው ዕርምጃ ነው ብለን እናምናለን፡፡ ይህን ሳናደርግ ቀርተን፥ እንዲያው በደፈናው፥ ሌላውን እየወቀስንና በሌላው እያመካኘን መኖር የለብንም፡፡ ያለፉትንና አሁን ያለውን የአምባገነን ሥርዓቶች እየወቀስን፥ እየኮነንን፥ እያወገዝን ብቻ መቀጠሉ ጭራሽ መፍትሄ አያመጣልንም፡፡ አንድ ትውልድ የራሱን የወቅቱን ችግር እራሱ የመፍታት ኃላፊነት፥ ግዴታና የታሪክ ተልዕኮው መሆኑን መረዳት መቻል አለበት፡፡ ወደ ምዕራባውያን ቢማፀኑ፥ ወደ ምሥራቅ ቢዞሩ፥ ወደ ዓለም አቀፍ ተቋማት ቢያንጋጥጡ፥ ወደ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ቢያጎነብሱ መፍትሄ አይገኝም፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ፥ በምፀት ኖረሽ በእንቆቅልሽ ተከፍነሽ ተቀበሪ የተባለች ይመስል፥ ዛሬም ከዚህ ክስተት ልትላቀቅ አልቻለችም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ከአምባገነን ሥርዓት ለመላቀቅ የደም መስዋዕት እየከፈለ ባለበት በዚህ የሞትና የሽረት ትግል ውስጥ መሆኑ ቢታወቅም፥ ትግሉን በሚገባ የሚያቀነባብርለትና የሚመራው ድርጅት እንደሌለ፥ ይኸው ገሃድ እየሆነ መጥቷል፡፡ ባለፈው በግንቦት 1997 ዓም በወያኔ ምርጫ፥ ማንም፥ ሳይቀሰቅሰው፥ ሳይመራውና ሳያግዘው ከዘረኞች አምባገነን አገዛዝ ለመላቀቅ የራሱን አማራጭ በመውሰድ የዘረኞችን አገዛዝ ፈንቅሎ ለመጣል ምን ያህል ኃይል እንደነበረው/እንዳለው ለዓለም አስመስክሯል፡፡ ያ ሕዝባዊና ሰላማዊ

ኃይል ግን፥ ሰላምን በሚጠሉ፥ ሕዘባዊ ኃይልን በሚፈሩ በወያኔ ነፍሰ ገዳዮች ተጻፈነ:: ለጊዜው! ደም በጠማቸው የአጋዚ ወታደሮች የሰላማዊው ሕዝብ በአደባባይ ደሙ ጎረፈ:: የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ድርጅቶችም ይሁኑ የዴሞክራሲ ሀገሮች የሚባሉትም ጩኸቱን ሊሰሙለት፥ አቤቱታውን ሊያዳምጡለት፥ ሰቆቃውን ሊያዩለት ፈቃደኞች ሆነው አልተገኙም:: የተቃዋሚ ድርጅቶችም ቢሆኑ ትግሉና ሕዝቡ በሚፈልገው ደረጃ አቀነባብረውና አመራር ሰጥተው አልተገኙም:: ዛሬ ይህ እንደሚሆን እናውቅ ነበር፥ እናም ተናግረን ነበር ማለቱ አይጠቅምም:: በአሁኑ ወቅት በሀገራችን የተከሰተው እንቆቅልሽና ምፀት፥ ከልክ ያለፈ መሆኑን የምንገነዘበው ሕዝቡ መሪ፥ የተቃዋሚው ክፍል ደግሞ ተመሪ መሆኑ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የመከራ ገመዱን በገዛ እጁ በጥሶ፥ የጭቆና ቀንበሩን ሰብሮ፥ ነፃነቱን ለማግኘት በሚያደረግው የሰላማዊ አመፅ ምክንያት፥ የወያኔ ነፍሰ-ገዳይ ሠራዊት በአደባባይ ጨፍጭፎታል:: ወደፊትም ይህንን ብሄራዊ ወንጀል በከፋ መልኩ እንደሚቀጥል ማንም ኢትዮጵያዊ አይጠራጠርም:: ይህንን የሕዝብ ጭፈጨፋ በዘላቂ መልኩ ለማቆም የሚቻለው፥ ከሕዝቡ ጎን ቆሞ የሕዝቡን የመከላከል ኃይል ሲያጎለብቱና ሲያጠነክሩ ብቻ ነው:: አንዳንድ ባዕዳን ደግሞ ተጨፍጫፊውን ሕዝብ እንደ አጥፊ፥ መለስ ዜናዊንና ነፍሰ ገዳዮቹን እንደ አልሚ እየቆጠሩ ነው:: ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መከሰትና መስፈን ሲታገሉ የተጨፈጨፉትን ሰላማዊ ዜጎች፥ የባንክ ዘራፊዎች ናቸው ተብሎ የተወሰደባቸውን እርምጃ ትክክል ነው ብሎ ቀደም ሲል መለስ ዜናዊ ሲናገር፥ ይህንን ሁኔታ አለማውገዝና ከሰማዕታት ጎን አለመቆም፥ በህሊና በኩል የሚያስከትለውን ወቀሳ ለጊዜውም ቢሆን እንተወውና በታሪክና በትውልድ ዘንድ የሚያስፈርድና የሚያስጠይቅ መሆኑን ግን ሳናስመዘግብ ማለፍ አንፈልግም::

ሕዝባዊ አመፅን አለመደገፍ ብሎም በመውገርገር ላይ ያለውን የመለስ ዜናዊን አገዛዝ አውሸልሽሎ ለማቆየት የሚደረገው ጥረት የኋላ ኋላ በኃላፊነት የሚያስጠይቅ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ያውቀዋል:: በዚህ የመከራ ዘመን በሚከፍለው የደም ዋጋ፥ ነገ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን እንደሚመሠርት ማንም ሊጠራጠር አይገባም:: ይህን ክስተት ለማምጣት በሚደረግ የትግል ሂደት ሊወሰድ የሚችለው ምርጫ ሁለት ብቻ እንደሆነ እናምናለን:: አንደኛውና ትክክለኛው፥ ከሕዝብ ጎን በመቆም አጋርነትን በተግባር ማሳየት ሲሆን፥ ሌላው ደግሞ የሕዝቡ አመፅ ተኮላሽቶ እንዲቀርና የወያኔ የዘረኛ አገዛዝ እንዲቀጥል በሚደረገው ሂደት የወንጀሉ አባሪና ተባባሪ መሆን ነው:: ከየትኛው ጎን የመቆሙ ጉዳይ የእያንዳንዱ ውሳኔ ነው:: ፈቅዶ በሚወስደው ውሳኔም ተጠያቂው ያው እራሱ ነው የሚሆነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን፥ አሁን የጀመረውን ትግል ሊያቆመው የሚችል ኃይል አለ ብለን አናምንም:: ዕርግጥ ዛሬ፥ ሕዝባዊው እንቅስቃሴ ጊዜያዊ ችንፈት፥ ወቅታዊ ፀገም ሊያጋጥመው ይችል ይሆናል:: ተዳፍኖ ግን ሊቀር የሚችል አይሆንም:: ይህንን መካድ ወይም አለመገንዘብ ማለት የታሪክን ሀቅ አለመረዳት ይሆናል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የሚፈልገው የማያወላውሉ፥ በዓላማቸው ፀንተው ቆራጥ ሕዝባዊ ውሳኔና አመራር የሚሰጡ መሪዎችን ነው::

እነዚህን አቅፎና ደግፎ ትግሉን መቀጠል አለበት፡፡ መለስ ዜናዊ ቀኑ እንደቀረበ ማንም ሳይነግረው እርሱ እራሱ የተረዳው ሆኗል፡፡ ሥልጣኑን ግን በሠላማዊ ሁኔታ ለሕዝብ ለማስረከብ ፈቃደኛ አይሆንም፡፡ ያ እስከሆነ ድረስ ደግሞ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊኖረው የሚችለው ምርጫ የያዘውን ሕዝባዊ አመፅ እያሰፋ እያጠነከረ መቀጠል ይሆናል፡፡ ይህን ሕዝባዊ አመፅ ለመደገፍና ከጎኑ ለመቆም ተልዕኳችን ስለሚያስገድደን የሕዝቡ ትግል እንዳይዳፈን የተቻለንን ሁሉ ከማድረግ የሚያግደን ምድራዊ ኃይል እንደሌለ ለሕዝባችን ቃላችንን እንደገና እናድሳለን፡፡ ለባላንጣዎቻችንም እያስረገጥን እንነግራቸዋለን፡፡ እሳት ቢዳፈን የጠፉ ለመሰላቸውም በትንታጉ-በነዲዱ እንገናኛለን እንላቸዋለን፡፡

የፈሰሰው የሕዝብ ደም መና አይቀርም!!
ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ሆነን ትግላችንን እንቀጥላለን!!!